ሠርካለም ፋሲል የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ባለቤት ነች። በ "እስኒል"፣ "ምኒልክ" እና "ሳተናው" ጋዜጦች አሳታሚነት ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ ለአንድ ዓመት ከ8 ወር በእስር የቆየች ሲሆን በግሉ ሚዲያ ባበረከተችው አስተዋጽኦ አሜሪካ ከሚገኘው ዓለም አቀፍ የሴት ጋዜጠኞች ማህበር ዓለም አቀፍ ሽልማት አግኝታለች።

ሠርካለም ፋሲል

ስለ እስክንድር ነጋ

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ታውቁታላችሁ። ከቅርብ ቀናት ወዲህ የመንግሥት ሰዎች "እስክንድር የሚባል ጋዜጠኛ አናውቅም" ቢሉም እናንተ ግን ታውቁታላችሁ። የምታውቁት ደግሞ ቢጋዜጠኛውቱ ነው። ከምርጫ 97 በፊት ለስድስት ጊዜ የታሰረው፣ ብዙ እንግልት የደረሰበት ለዓመት ከ8 ወር፣ ለወራተና ቀናት በተደጋጋሚ የታሰረው ቢጋዜጠኛውቱ ነው። ይሁንና ቢጋዜጠኛውቱ ብቻ ሳይሆን በበሳልና ጠንራራ ጽሑፎቹ ነው። እርግጠኛ የምሆነው "አናውቀውም ያሉት ወገኖችም ቢጋዜጠኛውቱ፣ በደፋር ጋዜጠኛውቱ ያውቁታል። በበም አናፈራቱ፣ መረጃ ሳይኖረው ለመታወም ብቻ የሚጽፍ በመሆኑ የሚያውቀው ማንም የለም። እስክንድር የዝና እና የጥቅም ፍላጎት እንደሌለው፣ ለመጻፍ ዋና ምክንያቱ እውነት ብቻ ስለሆነ ለ7 ጊዜ ፍርድ ቤት ቀርቦ አንድ ጊዜም ማስረጃ ተገኝቶብት አለማወቁ ዋና ምስክር ነው። ለሌሎ ቀርቶ ከጋዜጠኛውቱ ውጪ በ1997 ምርጫ ወቅት እሱን የማስረያ መንገድ ተደርጎ የተወሰደው "የቅንጅት ማስከበሪያ ኮሚቴ አባል ነሽ" የሚል ነው። ይሁን እንጂ ምንም ማስረጃ ሲቀርብበት ስላልቻለ በነጻ ተሰጥቷል።

በብዙ መልኩ ስለ እስክንድር ለመናገር ይቸገረኛል። ያልኩትንም ብል ሚስቱ ስለሆኖች ተብሎ እንደሚታሰብና ላልታመን እንደምችል አውቃለሁ። ይሁን እንጂ ስለ እስክንድር ለመናገር መረጃ ማስባሰብ ብዙ አያሻም። እንኳን ስንሰሰብ አስምር ስፍር ቤትም ማስጋገውን አቅርቦ ነጻ ወጥቶቢታል። ሆናም እስክንድር ሰድሰኛ አይመስለኝም። የመረጠው መንገድ ለሌላም ሆነ ለእኛ ለተተከዩ አደገኛ ነው። እነዚህ ሁሉ እስሮችና እንግልቶች ወቅት እየጠበቁ እንደሚመጡብት ጠንቀቅ ያውቃል። በእኔ እምነት እስክንድር ያላወቀውና የተታለለበት ጊዜ የሚመስለኝ "ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ተከብሯል" ሲባል የተማረባትንና በምኞት የኖረበት አሜሪካን ትቶ ወደሚወዳት ሃገሩ በመመለስ የመጀመሪያዎቹን "ኢትዮጲያ ጋዜጣን ሲጀምር ነው። ይህ ከእኔ እንጻር ሲታይ ነው። እስክንድር ግን ሃሳብን በነፃት የመግለጽ መብት ካለ በሀገር ዲሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር ቢኖርም ለሀገሩ ሠተዘ እንጂ ስራት የሚያስብ አይደለም።

እስክንድር ሮጌል ጥቅሙ ጉጉት ቢሆን ኖሮ ማስተራፊን ከአሜሪካ ይዛ መጥቶ የግል ጋዜጣ ለመጀመር ባላሰበ ነበር። ጋዜጣ የማሳተሙን ሥራ ጀምሮ ብዙም ሳይቆይ ነው እዚህ ሀገር የሚባለውን ያህል ሃሳብን በነፃት የመግለጽ መብት እንደሌለ የተረዳው። ከዚያም በኋላ የሚያየውን ላለመናገር፣ ያለውን ላለመጻፍ፣ ይልቁንም በሌላ የሥራ ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ ሀላፊነቱንና የወጥታውን ሕይወት መኖርም ይችል ነበር። እስክንድር ለመኖር ጋዜጣ ማሳተም ወይም ችግር ሲያመጣቸት የሚችለውን ሥራ መሥራት አይጠበቅም። የመኖሪያ አጡት ችግርም የለበትም። እንደ ሚስቱ እና የልጁ እናት የማውቀው ነገር ለእስክንድር መኖር ማለት እውነት ለመሰለው ነገር ግንዛቤንና ልቡን መስጠት፣ በዚህች ሀገር ላይ ሀላፊና ያጣማሬሊ፣ ሰዎች በምናቸውም የማይከፈሉበት ነጻ ምድር ተፈጥሮ መኖት ነው። ይህን ለመፍጠር ብዙ መስዋዕትነት እንደሚያስከፍል ያውቃል። ሲከፍልም ኖሯል።

እንዲህ እንዳሁት "ዝብርተኛ" የሚል ስም ሳይለጠፍበት በፊት... መቼም ጋዜጠኛው እስክንድር ነጋ፣ የሚውቀውና ሠላማዊው እስክንድር ነጋ በዚህ ስም ሲጠራ ከልቤ አዘንስሁ። በሌላ በኩል "ዝብርተኛ" ያለው የሚወደውና በብሄሩ የታገለለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለመሆኑ እጽናናለሁ። የግላት ታጋይ ለመሆን የግዴ ጠመንጃ አንስቶ ጫካ መግባት የሚያስፈልግ ካልሆነ በቀር እስክንድር ለኔም ሆነ ለሚያውቁት ጠንራራ የግሉት ታጋይ ነው። በትግል ውስጥ ደግሞ ብዙ ስም መጥሩቶች፣ ብዙ ስያሜዎችና መንገላታቶች ይኖራሉ። እስክንድር ይህን እየከፈለ ነው የመጣው።

ከመታሰሩ ወራት በፊት እሱ ራሱ እንደገለጸው የፈደራል ፖሊስ ምክትል ከምሽር ቢሯቸው አስጠርተው "ጓርምጃ እንወስድብሃለን" ብለውታል። "ጓርምጃ እንወስድብሃለን" የሚለው እስክንድር ህዝብን ሳለማሽከር አስገዝ ጋዜጣ ላይ የጻፈው ቃል ነው። አሱኝ ብሎ ለኔ የነገረኝን ቃል ግን እሱና ጋሳፊው ያውቁታል። ምንም እንኳን ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የተሰማውን፣ መረጃ ያለውንና እውነት ነው ብሎ ያመነበትን ከመግለጽ ወደኋላ አይልም ቢባልም ጋሳፊው የተናገሩትን እንዳለ ለመጻፍ ድፍረት አጥቶ ወይም ከፊፊው የተለየ ነገር ያደርገኛል ብሎ ስራሱ ፈርቶና ሰግቶ አይደለም። የተባለውን ቢጽፈው በህዝቦች መሃል አመጽ የሚያስነሳ፣ ባያስነሳም ቁም የሚያስይዝ ሲሆን እንደሚችል ስለመነ ነው። በዚትኛውም መልኩ ደግሞ እስክንድር ሠላማዊ ትግልን ነው ምርጫ ያደረገው።

ምክትል ከምሽሩ ቢሯቸው ባለጠሩት ጊዜ ያሉትን ያሉት በሽብርተኝነቱ ሳይሆን ቢጋዜጠኛውቱ ነው። በጨፈራቱ ነው። ያስጠከሎቱትም፣ "አንተን ማስር ስልትተናል" ያሉትም በአሸባሪነቱ አይደለም። ከሽብር ተግባርህ ተቆጠብህም አሉሉትም "ጎተጻፍ" እንዳሉት ባይጽፍ ይሆን ስም እንደማያኝ አምናለሁ።

ባጂ አብሯት እንዲኖርና በዋስር ቤቱ አብራውም እየታሰረች፣ ስንትም እያስከፈለች መመላለስ እንደማትሻ ሚስት እስክንድር ነጋን እንዳይጽፍ መንገርና ማስገደድ ሳይሆን መለመን ነው ያለብኝ። እርግጥ ነው ባስገድደውም ብለምነውም ከዓላማው ለመልለው እንደማልችል አውቃለሁ። እንኳን አድጋና ትልቅ ሰው ሆኖ በፍቅር ያገኘሁት ሚስቱ ቀርቶ ምንም ሙተኪያ ሳይኖራቸው አንደ አሱን ብቻ የወለዱት እናቱም በቻሉት ሁሉ ሲለምኑት፣

ከዚት ሲጠሩ በጋዜጣ አሳታሚምቸና ባሃኑት መንገድ ሁሉ እየሔዱ "ልጆች እስክንድርን አይታችሁታል?" እያሉ የሚያስሱትና የሚማፀኑት እናቱ እንኳን ከዓለማው ሊመልሱት አልቻሉም።

እስክንድር እኔንም፣ እናቱንም፣ ወጋጅ ዘመዶቹንም ባይሰማ እንኳ ራሱ ለእናቱ አንድ እንደሆን ሁሉ ለእኔና ለአሱም አንድ የሆነውን የአምስት ዓመት ልጁን ናፍቆትም በደመሳፍስ መማፀኑ ሲሰማው በተገባ ነበር። "አባባ ስም" እንደሰው ሁሉ እርጭ ብለህ ተተምጠህ አታሳድጉኝም?" እንደሚለው ማሰቡ አልቀረም። ይህ ስለሚሰማውም ይሆናል የአምስት ዓመት ልጁን አቅር አያሻሽው፣ ልክ እንደትልቅ ሰው ሲያናግረው አሰማዋለሁ። "ናፍቆት ታሳገኛኛለህ" ይለዋል። "ታሳገኛኛለህ ናፍቆቱ እወድሃለሁ! እወድሃለሁ! እንደ አባት ከጉንህ ሆኜ ባሳድግህ ደስ ይለኝ ነበር። ግን የምችል አይመስለኝም። የማሳድገህ አይመስለኝም ይለዋል። ሀዘኑ አባቱ ያለው ምን ማለት እንደሆነ ቢገባው ምን ይሰማው ይሆን? ግን እኳ ጋም አልገባው። እስክንድር ልጁን በሥሙም እንደማያሳድገው ያውቃል። ነገር ግን ለእስክንድር የሀገሩ ነገርና የህዝቦቹ ነገሮት ከልጁም በላይ እንኳ ዋጋ ያላቸው ናቸው። ለዚህም ይሆናል "ክሽሽ ለናፍቆት አንቺ ኑረሽ። አደራሽን በቻልሽው ሁሉ አሳድገሽ ሰው አድርጊው" ይሰኛል። በዚህ አባባሉ ከተገመገሙ ሁ "እኔ እንደሆን አባቱ ሆኜ አቅፌ ሳሳሳድገው እችላለሁ። አንቺ ባትኖሪ እንኳ እናትሽ አሉሉት። አሳቸው ያሳድጉታል" ይለኛል።

ናፍቆት አድጉ ትልቅ ሰው ሲሆን ያኔም ይህቺ ሀገር እንዲሁ ከሠገች ታጋይ እንደሚሆን አምናለሁ። እስክንድር አስመስሎ፣ የተገኘውን በሉቶ የሚያድር ልጅ እንዲኖረው አልመኝለትም። በእስክንድር ይህን መንገድ መምረጥ እኔም የሴታዊ ሰብ ብሆም እሱን የማይተካ ልጅ እንዲኖረው አልመኝለትም። እውነትና ፍትህ በዚህች ሀገር ከሌሉ እስክንድር ከአንግዲህ ልጁን ሳያየው ይችል ይሆናል። ግን ደግሞ ይህ ልጅ በዚህ ሥርዓት እስር ቤት ውስጥ የተወለደ ነው። የአምስት ዓመት ልጅ ያየውን በአዕምሮው መቅረጽ ይችላልና አባቱ ራቱ በፖሊሶች ካብና ሲታሰረና ሲንሳታ አይቷል። አባቱ ራሱ ሕሙሙ የተወለደበት ወህኒ ቤት መግባቱን እየየ ነው። ማንበብ ሲችል እነዚህ የሚጻፉትን ጽሑፎች ሁሉ ያነባል። ያኔ አባቱ በአደወት ባይኖር፣ እስር ቤት ቢሆን ወይ ተሰቶ አስሮት ቢሆን የማን ልጅ እንደሆነ ያውቃል። ከዚህ ልጅ ምን ይጠበቃል?

አባቱን በቴሌና አስረው ባነጻዩ ሲቀርቡት ፎቶ ሲያሳሱት ሕሙሙ መሬት ላይ ወድቆ እያሱሰሰ ሲንዳባለል ቢያንስ እንኳ ከመገበል አሉንም አብረው ባነጻዩ ይቀርጹታል። ፎቶ ያሳሱታል። ይህ ዘግናኝ ድርጊት ለዞትኛው ሁኔታ መረጃ እንደሚሆን እነሱ ናቸው የሚያውቁት። የሕዝን ልጅ ለትሰና ዋይታ ለዞትኛው ትውስታ እንዲሪዳ እንደተቀደ አለውትም። መቸም እዚህ ሰዎች ሁሉም ባይሆኑ የተወሰኑት ቢያንስ ከመቃከላቸው አንዱ ልጅ አለው። ልጅ ባይኖሯቸው እኳ ሰብአዊ ፍጠርነት አላቸው። እስክንድርን እንዳሉት "ዝብርተኛ" ቢሆን እኳ ናፍቆት ስለሽበር የሚያውቀው ነገር የለም። ለምን ፍቅር፣ ደስታ፣ ጨዋታ በሚፈልግ ሰድሚው ሽብር እንዲደርስበት እንደተፈለገ አይገባኝም። ያልታደለ ሕገ!

የናፍቆት አባት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እንደተባለው ሽብርተኛ እንዳልሆነ ከማንም በላይ፣ ከእኔ ከሚሉትም እኳ በላይ እግር ከአግር የሚከተሉት የደህንነት ሰዎች ያውቁታል። አንድ ቀን ማንም ሳይሆን ራሳቸው የደህንነት አባሉ ለእስክንድር ንጽሕና እንደሚመስክሩ አውቃለሁ። ከቤት ሲወጣ ከእኔ ጋር እንለያያለን። ከማን ጋር እንደተገናኘ፣ ምን ሲያደርግ ቆይቶ እንደመጣ ራሱ ካልነገረኝ በቀር አላውቅም። የደህንነት አባሉ ግን የቤቱን ዙሪያ ከበው ስለሚውሉ፣ የትም ቢወጣና ቢገባ አብረውት ስለሚንቀሳቀሱ፣ ይህን ያህል ነገትል ካደረገባት ስልኩንና ሌሎች የግንኙነት መረቦቹንም መቆጣጠራቸው እንደማይቀር ስለማምን እስክንድር ያየውን ከመጻፉ በቀር በየትኛውም የሽብር ተግባር ላይ እንደሌለበት እነሱ ያውቃሉ።

እስክንድርን ከዓለማው የምንገትተው ሰው አይደለሁም። ይሁን እንጂ ከግራና ከቀኝ "ሸረ ተው በይው!" የሚለው ጉተጉታ ሲበዛብኝ፣ የደህንነቶቹን ነገትል ሳየው፣ አቦሀን ቤት ጉበተው አብረውን አልተቀመጠም እንጂ በመልክ ሚምር እስክንስያቸው ስለሚከታተሉት "ስኩቲ አረፍት ስጣቸው። አንተም አረፍ በል" ስሰው "እንቺም? አንቺም እንዲህ ነው የምትይኝ? እግዚህ ማነው ለኔ ያለኝ?" ነው የሚለኝ። እኔም አለኩቸግረውም። ደግሞም ሚስቱ ስለሆኝ፣ እሱም እንደሚለው አንድ ልጃችን ስለሚያሳዝኑኝ እንጂ ዓላማውን ሳልደግፈውና ሳልከራ ቀርቼ አይደለም። እስሩን፣ ስጋቱን፣ ፍርሃቱን ስምጀዋለሁ። እስክንድር ከእንግዲህ ከእስር ቤጠ ጎጠ ከመሄድ፣ ያየውን እንዳለየ የሚሆን፣ ፈሪና ልምጥምጥ እንዲሆን አልፈልግም። ምናልባትም ብፈልግ እንኳ፣ እንደማይሆን ስለወቅሁ ይሆናል የእውነት፣ የፍትህ እና የነፃት ጉዳይ ለእስክንድር ትልቅ ዋጋ ያላቸው ናቸው። ብዙ የተንከሳተቸቸው፣ ሁሉት መልክ ያወገዛቸው ቁም ነገሮች ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አቋርጠው ማክ ጉበተው እንደታገሉት ሁሉ እስክንድርም ያጣውን አጥቶ፣ ከደረሰበት በላይ መሳራ በደርስበትም እንዳይታገል ማድረግ አይቻልም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ እና የእስክንድር የትግል ስልቶች የሚለዩት አሳቸውና አጋሮቻቸው ጠመንጃ አንስተው መዋጋታቸውና እስክንድር ግን ፍፁም ሠላማዊ የሆነውን ትግል መምረጡ ነው። ■